# ሕዝብን ማዘናጋቱ ቢያበቃሳ?

## ይድረስ ለእነ ብርሀኑ ነጋ፤ አንዳርጋቸው ዕጌና ኤልያስ ክፍሌ

ከ   መላኩ ወንድም አገኝ

ይህን ፅሁፍ ለመፃፍ ያነሳሱኝ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ዶክተር ብርሃኑ ነጋ በቅርቡ በኒው ዮርክ ባደረጉት ንግግር የመለስ አገዛዝ ለአምስት ዓመት በስልጣን ቀጥል ብለነው ነበር ያሉት፤
2. በኢትዮጵያን ሬቪው ድህረ ገፅ የተወሰኑ የቅንጅት መሪዎች ወደ ባዕድ ሀገር መውጣታቸውን አስመልክቶ የሚደረገው ቡራ ከረዩ፤
3. የቅንጅት ዋና መሪ ኤንጂነር ሐይሉ ሻውልን ለማስወገድ እየተካሄደ ያለውን ሴራ በተመለከተ በወያኔው አይጋ ፎረም ሳይቀር እየተፃፈ ያለው፡፡

በበኩሌ በቅድሚያ በኤልያስ ክፍሌ ቀልድ አይሉት ምፀት ድህረ ገፅ ልጀምር፡፡ በበኩሌ ይህ መሰሪ ግለሰብ ጊዜ ይስጠን እንጂ ለማን እንደሚሰራ ይጋለጣል ብዬ አምናለሁ፡፡ ቅንጅትን ደጋፊ መስሎ በስልት ለክፍፍሉ እንደሰራ ሁሉም የሚያውቀው ነው፡፡ የወያኔ ባለሟል ናቸው የሚባሉትን እየደገፈ፤ ሻዕቢያና ኦነግን አልፎም የሶማሌ አክራሪዎችን ጀግና እያለ (ትላንት ጠላቶቼ ናቸው ይል ነበር!)፤ ክህደቱ ልደቱን ማንዴላ ብሎ ሲያሞግስ እየቆየ ፤ የሙሴ ተገኝን አርበኞች ግንባር በጭፍን እያሞገሰ ፤ ወዘተ ውዥንብርን ሲነዛ የከረመ ይህ ከፋፋይ ፀረ ህዝብ በሰሞኑ ደግሞ ኢንጂነር ሀይሉን ወደ ጎን የተወውን የቅንጅት አጠያያቂ ልዑክ በዋሺንግተንና ሎንዶን ሚሊዮኖች የተቀበሏቸው በማስመሰል ድል ድል ሊለን ሞክሯል፡፡ ብርቱካን ሚድቅሳና አብረዋት የመጡት ሁሉ ሆኑ ወደ ለንደን የተጓዙት ሌሎቹ ሁሉም ለወያኔ በሆነው ምክንያት ተሸንፈው ይቅርታና ምህረት ጠይቀው ከእስር የወጡ ናቸው፡፡  የማይደበቀው ሀቅ ወያኔ እንዳዋረደንና እንደተመፃደበቅን ነው፡፡ ድል አልተጎናፀፍንም፡፡ ብርሃኑ ነጋም ቢሆን ያው ነው፡፡ ለወያኔ አምስት ዓመት ሰጪ ማን አደረገው? ብርሀኑና በየነ አይደሉም እንዴ ከቪኪ አሜሪካዋ ጋረ ሆነው የሕዝብን የሙት ከተማ አድማ አኮላሽተው ትግላችንን አፈር ያበሉና ወደዱም ጠሉም ለወያኔ የጠቀሙ? ድህር ገፆች ብርቱካን የቁንጅና ውድድር ወይ ሎተሪ እንዳሸነፈች ይመስል በመኪና አጠገብ ፎቶዋን አሳይተውናል፡፡ ሀፍረት! ቅንጅትን ደግፈው የሞቱት እህቴና ወንድሜ፤ እነሺብሬ ግን ምን ይሆን የሚሰጣቸው? ፖለቲካና ትግል ቀልድ ሆነ? በሺ የምንቆጠር በባዕድ መሪዎችን ተቀበልናቸው በሚል የድል ጩኸት ብጤ ማሰማቱ ምን ይባላል? ይህ ሁሉ ጫጫታ ነገ ተኖ መጥፋቱ መቅረቱ ብቻ ሳይሆን ያለውን የተቃዋሚ ቡድን ቀውስና ከባድ ችግር የሚሸፍን ሊሆን አይችልም፡፡ ስለ ችግሩ አቶ በድሩ አደምም ፕሮፌሰር መስፍንም በሚገባ ገልፀውታል፡፡ የእነ ኤልያስ ክፍሌ አደናጋሪ ጩኸትና የእነ አንዳርጋቸው ፅጌ ( ለመሆኑ የዋሺንግተኖቹን ይልማ አዳሙና አብርሃም በቀለ የማናውቃቸው ሆነን ነው!) መሰሪ ዲስኩር ዛሬ ዋጋ ቢስ ነው፡፡ ትግሉ ወደፊት ይግፋ ካልን ሀቁ መነገር አለበት፡፡

መቀበል ያለብን እውነቱ ምንድነው? ከወያኔ ደጋፊው አዲስ ፎርቹን መጥቀስ ያሻናል? ብርሀኑ ነጋ የቅንጅት 8 ነጥብ የሚለው ዋጋ ቢስ ጫጫታ ዛሬ መሰማት ነበረበት? ቅንጅት በሚል ባለፈው ሰሞን በሀገር ቤት የቀረበው የሰባት ነጥብ ሰነድ በወያኔ በራሱ የተፃፈ ነው ቢባል ስህተት ነው? ምን ሁኔታ ላይ ነን?

- ተቃዋሚ በአጠቃላይ ብቻ ሳይሆን ቅንጅት በተለይ በተከፈፋለ ሁኔታ ላይ ነው፡፡
- ብርሃኑ ነጋ የተሰማራበት ተልዕኮ ከቅንጅት የተፃረረና ጎጂ መሆኑን እነ አቶ በድሩ አደምም ገልፀውልናል፡፡
- አንዳርጋቸው ፅጌ ያለው አጀንዳ ወያኔያው መሆኑን ብዙዎች ተችተውበታል፡፡
- ፕሮፌሰር መስፍን፤ አቶ በድሩ አደምና ሌሎች ከቀስተ ዳመና ወጥተዋል፡፡
- በአሜሪካ አስተባባሪነት ከወያኔ ጋር ዳግም በምርጫ እንሳተፍ የሚሉት ክፍሎች በእነ ብርሀኑና ሌሎች መሪነት እየተደራጁ ነው፡፡
- ለዚህ ክህደት ተቃዋሚ ይሆናሉ በተባሉት በኢንጂኔር ሀይሉ ሻውል፤ዶክተር ታዬ ወልደሰማያትና ኢሕአፓ ላይ ዘመቻ ተከፍቷል፡፡ በዘመቻውም እነ ኤልያስ ክፍሌ፤

ከረንት አፌይርስ ፓልቶክና ሌሎችም ግንባር ቀደም እንዲሆኑ መመሪያ ተሰጥቷቸው እየሰሩ ነው::

- ለማደናገር እነ ብርሃኑ ነጋና ሆኑም ሌሎቹ ፀረ ወያኔ መስለው በመጀመሪያ ሰሞን ሊቀርቡ መሞከራቸው የሚጠበቅ ነው::
- የቅንጅት መሰረታዊ ዓላማ የሚጠበቀውና የሚንፀባረቀው የስልጣን ጥመኛና የአሜሪካ ሎሌ በተባሉት በነ ብርሀኑ ወይም የኤልያስ ክፍሌ "ጀግኖች" አንጃ አይደለም::

በርበሬ ዕጣን አይሆን፤ ነገር ስልጣን አይሆን ተብሏል:: በዋሺንግተንና ለንደን ጩኸት በረከተና 77 ሚሊዮን ሕዝብ ፈነደቀ ማለት ያው ወያኔ የካቲት 12 የሕዘብ ፌንጠዚያ ቀን እያለ ራሱን እንደሚያታልለው ነው:: በአሁኑ ጊዜ ተቃዋሚ ሀይሎች በከባድ ሁኔታ ውስጥ ገብተዋል እንጂ ድል በድል አይደሉም::አይደለንም:: በዋሺንግተን ሳይሆን መዋደቁ በሀገር ቤት መሆን ነበረበት:: መኪና ሽልማቱና በባዕድ ሀገር እስክስታው ቅር አይበለንና ዋጋ የለውም፤ በገዋ ጫጫታ ነው:: ምን ያህል ወያኔ እያፌዘብን እንደሆነ ደግሞ ኤልያስ ክፍሌን ብቻ ሳይሆን አይጋ ፎረምንም ማየቱ ይበቃል:: የተወናበደ ሁኔታ በመስፈኑ ማን ጀግና ማን ባንዳው የጠፋን ይመስላል:: የዋሺንግተን ሚሌኒየም የተከበሩ እንግዶች የማርያምን ቤተ ክርስቲያን ሳይቀር ለወያኔ ያስረከቡት የዶክተር አክሊሉ ዓይነቶቹ ናቸው:: ኢትዮጵያ የጀግና ሀገር ናት:: ይህን የዘነጉት ክፍሎች ወር የተሳሩትን ወጠጤዎች ማንዴላ ብለው ሲጮህቡን ነበር:: ዛሬ ደግሞ የሀገር ጀግኖች በእውነቱ እነ ማን ናቸው? ለወያኔ ግዛ ፤ ተጫማሪ አምስት ዓመት በስልጣን ቀጥል ብንለው አሰረን ያሉና ወዲያው ማረን ብለው የወጡት ወይስ ዛሬም በእስር የሚማቅቁት? ለፀረ ህዝብ አንሰግድም ብለው የተሰዉት ወይስ መለስ ሲደነፋ ብርክ የያዛቸው? ለሆዳቸው ያደሩ ወይስ ለህዝብና ለሀገር ህይወታቸውን የሰጡ? ዛሬም ባዕድ ትዕዛዝ ትግል ሊያኮላሹ ቪዛ የተሰጣቸው? በጣም የሚያስገርመው ደግሞ ልሂቅና ምሁር ነን እያሉ የገማ የገለማውን በአዲስ ግኝት መልክ ሊሸጡልን የተነሱት ናቸው:: አዲስ ትልምና ዕቅድ የሚሉት ያው በዚህም ሆነ በዚያ ለወያኔ መንበርከኩን ነው:: በመጪው ምርጫ መሳተፍ፤ ከወያኔ መደራደር፤ የብረት ትግሉን መተው፤ወያኔ ሲገርፈን በዝምታ መቻል፤ በአጭሩ ክህደትና ባንድነትን አዲስ ብሎ መቀበል ማለት ነው:: ባንዳ ለመሆን ዶክትሬት አያሻውም:: የኢትዮጵያ ምሁሮችና ተማሪዎች ታሪክ ሀገርን አኩሪ ሆኖ ሳለ የዘመኑ ደግሞ ባንዳነትን ዕውቀት አድርጎ ከተነሳ ዝም ልንለው አይጠበቅም:: ይህ ክህደት በማንም ድርጅት ከተንፀባረቀ ሊወገዝ ይገባዋል:: ድርጅቶች ራሳቸውን አማፃደቀው ሰማይ ስለሰቀሉ ሲቆሸሹ ለማጠብ ልናወርዳቸው አንችልም ማለት አይደለም:: ቅንጅት መንፈስ ነው (ይህ ምን ማለት ይሆን?) ወይም በደፈናው የመላ ህዝብን ድጋፍ ያገኘ ነው(!) ስለተባለ አፋችን ሊለጎም አይገባም:: ህዝብ ነው ባለስልጣን፤ ህዝብ ነው ከሃሊ:: በትግል ገና በበቂ ያልተፈተኑት ቀርቶ በትግል ዓመታት ያሳለፉትም ቢሆኑ ከትችት ነፃ ሊሆኑ አይችሉም::

የሀገር ጉዳይ ባልነበረ በኤልያስ ክፍሌና መሰሎቹ ዕሁፎችና ልፈፋዎቹ በቀለድኩኝ ደስ ባለኝ ነበር:: የሰሞኑን የድህር ገፆቻቸውን ጫጫታ አንቡት እስቲ ወገኖቼ:: ድል በድል ሆነናል:: ከመቶ ሺ በላይ ዜጋ ባለበት ዋሺንገተን ሺ ያህል ወጥተው የብርቱካንን ልዑክ ቡድን ስለተቀበሉና በሊሞዚን ሲጓዙ ዕልል ስላሉ ወያኔ አፈር በላ ሊሉን ይቃጣሉ:: ይህ ቀልድ ለማን ይጠቅማል? ወያኔ ይስቃል ወይስ ይሸበራል? ድል ገና ነው:: ቅንጅት ጤነኛ አይደለም:: ታሟል:: ተቃዋሚ ሀይሎች አልተጠናከሩም:: ምህረት ጥየቃው ድላችን ሳይሆን ባለው ሁኔታ ሀፍረታችን ነው:: ኤኤፍዲ የምንኮራበት ሳይሆን የምናፍርበት ነው:: ፀረ ኢትዮጵያ ክንዋኔ ነው:: በመጨናገፉ ልንደስት እንጂ ኢትዮጵያኖች እንደሚመኙት ነፍስ ልንዘራበት አይታሰብም:: እነ ብርሀኑና መሰሎቹ ጀግኖቻችን፤መሪዎቻችን አይደሉም:: የህዝብ መሪ ለባዕድ አይታዘዝም:: ለገዢው ክፍል አይንበረከክም:: የፈሪ መሪ የለም--ለፈሪ መንጋ ካልሆነ:: መሪዎቻችንን ገና አላወቅንም፤አላገኘናቸውም:: አንወናበድ:: አንደናገር:: በዋሺንገተንና በሎንደን አውሮፕላን ማረፊያዎች የተደመጠው ጫጫታ ወያኔን ቅንጣት አይጎዳውም:: ነገም በየስብሰባ አዳራሹ ቪቫው ቢበራከት ፋይዳ ቢስ ነው:: አደብ ገዝተን፤ ጭምት ሆነን፤ ስህተት አምነን፤ ልዩነትን መደበቅ ሳይሆን በግልፅ ውይይት አስወግደን፤ ማን ፀረ ወያኔ ማን የወያኔ አጋር መሆኑን ለይተን፤ ማን የአሜሪካ አጎግበጓቢና ታዛዥ ማን የኢትዮጵያ ተሟጋች መሆኑን ለይተን፤ ከ ኤልያሳዊ ጎጂ ባዶ ጫጫታና ድንፋታ ርቀን፤ አሰመሳይ ሰርጎ ገቦችን አሸቀንጥረን፤ ድክመታችንን በድፍረት አውጥተንና መርምረን፤ መፍትሄ ፈልገን፤ ሀቀኛ ሀገር ወዳዶችን አስተባብረን፤ የግል ዝ ና ስልጣን ጥምን ገድበን፤ የኢትዮጵያን ጥቅም አስቀድመን ልንታገል መቻል አለብን:: ሌላው ሁሉ ከንቱ ነው:: ዋናው ህዝብ ያለው ሀገር ቤት ነው:: 77 ሚሊዮኑ

ድህው ኢትዮጵያዊ ፡፡እነ ብርሃኑ፤ አንዳርጋቸው፤ኤልያስና መሰሎቻቸው የረሷቸው፤የናቋቸው፤ በፈረንጅ ምሁር ያልተባሉ፤ ዋሺንግተንና ለንደን ያልተጓዙ ኢትዮጵያውያኖች፡፡ ከእነ በረከት ስምዖን ጋር ያልጨፈሩ፤ መኪና ሊሰጣቸው ሊነዱ ቀርቶ እግራቸው የቆረፈደና የተሰነጣጠቀ፤ በዴዴሳና ዝዋይ በየጉድጓድ እስር ቤት መከራን የሚቀበሉ፤ ለፍርድ ቤት ያልበቁ፤ የት እንዳሉ ድራሻቸው የጠፋ፤ 20 ሰላሳ ሰው ክትፎ በድንገት ቤታቸው ሊጋብዙ ቀርቶ ቁራሽ ዳቦ ያረረባቸው፤ ሚሌኒየም ተብዬውን በባዕድና ሀገር ቤት ሆቴሎች በፈንጠዝያ ሊያሳልፉ ቀርቶ መልካም አዲስ ዓመት ማለቱ ማፌዝ የሆነባቸው የኢትዮጵያ ሀቀኛና ብርቅዬ ልጆች፡፡ ባለ ቪላ ሳይሆኑ መንገድ አዳሪዎች፤ ጥግበው አዳሪ ሳይሆኑ ረሀብተኞች፤ ሀቀኛ ኢትዮጵያውያን፡፡

ተቃዋሚ ነን ባዮች ገፃቸው ህዝባዊ መሆኑ ቀርቶ ዛሬ አዲስ አበባ መጣሁ ቀረሁ በሚለው ደካማ ውሃ እንኳን ሳይታጠብ  እነ  መለስን ከመሰለማ ነገሩ ተባለሽቷል ማለት ነው፡፡

ህዝብን ማደናገሩ ያብቃ! እውነቱ ይነገር! ባንዳ ጀግና አይባል!  የወያኔ ባለሟሎች ተቃዋሚ አይባሉ!! ጎራችን ይጥራ!!! ዓይን ካላዩበት ግንባር መባሉን አንርሳ!!